እርቅ ለሰማይና ለምድር

ዓለምአየሁ አ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሃገሪቱ የክርስትና ታሪክ ያህል እድሜ ያስቆጠረች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም አንጋፋ ሃይማኖታዊ ተቋም ነች። ቤተክርስቲያኗ በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ተቋም ብቻ አይደለችም። የሃገሪቱ ስነጥበብ፣ ስነህንጻ፣ ታሪክ፣ ሳይንስ፣ ፍልስፍና፣ . . . መሰረት ነች። የኢትዮጵያን የማህበረሰብ እድገትና የስልጣኔ ታሪክ ሂደት ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነጥሎ መመልከት አዳጋች ነው።

የኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖትም የእስልምናን ታሪክ ያህል ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ነው። ኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖትን በመተዋወቅ ከመካከለኛ ምስራቅ ሃገራትም የምትቀድም፣ ቀደምት እስላማዊ ሃገርም ነች። የእስልምና ሃይማኖት እንደ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ሁሉ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ፣ ስነህንጻ፣ ታሪክ፣ ፍልስፍና ውስጥ ጉልህ ድርሻ አለው።

ቀደምት የኢትዮጵያ የስነመለኮት ልሂቃን፣ የስነፈለክ ተመራማሪዎች፣ ፈላስፎች፣ ጸሃፍት፣ የሙዚቃ ጠቢባን ወዘተ የሁለቱ ሃይማኖቶች ትምህርት ቤቶች ውጤቶች ናቸው። በአጠቃላይ የሃገሪቱ የእውቀት መሰረት የሁለቱ ሃይማኖቶች ትምህርት ቤቶች ናቸው ማለት ይቻላል። እነዚህ ሃይማኖቶች ኢትዮጵያውያን በመቻቻልና አብሮ በመኖር ስነምግባር እንዲኖታነጹ በማድረግ ረገድ ትልቅ ድርሻ ተወጥተዋል። ይህ የመቻቻል ስነምግባር የሃገሪቱ ሰላም መሰረት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ፊውዳል መሳፍንቶች እንጂ ህዝብ በሃይማኖትም ይሁን በማንነት የተጋጨበት ጊዜ የለም። የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታይ ኢትዮጵያውያን ለነጻነታቸው ቀናኢ ሆነው እንዲታነጹ የማድረግ ድርሻም ነበራቸው።

በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታትን የተሻገሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ምንም ፈተና አልገጠሟቸውም ማለት ግን አይቻልም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የነገስታቱን ህጋዊነት የማረጋገጥ ድርሻ ይዛ የመንግስት ሃይማኖት ሆና በቆየችባቸው ዓመታት የእስልምና ሃይማኖት እውቅና ተነፍጎት የነበረ መሆኑ አይካድም። ነገስታቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የእስልምና ተከታዮች መኖራቸውን መቀበል አልፈቀዱም ነበር። የእስልምና እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያውያን ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሙስሊሞች ነበር የሚባሉት። ይህም ሆኖ ግን በሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች መሃከል ያለው መቻቻልና መከባበር ጸንቶ ዘልቋል።

ኮምኒስታዊው ወታደራዊ መንግስት በአጠቃላይ ለሁሉም የሃገሪቱ ሃይማኖቶች እውቅና ነፍጎ የዜጎችን ሃይማኖታዊ ነጻነቶችን ገድቦ ነበር። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 2ኛው ፓትሪያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ በወታደራዊው ደርግ መገደላቸው ይታወሳል። በተለይ ከኦርቶዶክስና ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም ከእስልምና ውጭ የሆኑ ሃይማኖቶች ተከታዮች ላይ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ገደብ ተጥሎ መቆየቱ ይታወቃል። በኮምኒስታዊው ስርአት ዜጎች በሚከተሉት ሃይማኖት ምክንያት ብቻ ታስረዋል፤ ተገርፈዋል፤ ተገድለዋል፤ ተሰድደዋል።

ያም ሆነ ይህ፣ ባለፉት ሁለት ተኩል አስርት ዓመታት በሃገሪቱ የሃይማኖት ነጻነት በህገመንግስት ተረጋግጧል። በዚህ የሃይማኖት ነጻነት አተገባበር ላይ ግን ችግሮች አልጠፉም። በ1984 ዓ/ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 4ኛው ፓትሪያርክ አቡነ ማርቆርዮስ ሃገራቸውን ለቀው ተሰድደዋል። አቡነ ማርቆርዮስ የሃገር ቤቷን ቤተክርስቲያን ትተው መሰደዳቸውን ተከትሎ 4ኛ ፓትሪያርክ ተቀብቷል፤ አቡነ ጳውሎስ። ይህ ሁኔታ የቤተክርስቲያኗ ራስ የሆነውን ሲኖዶስ ሁለት ቦታ ከፍሎታል፤ የሃገር ውስጥና የውጭ ሲኖዶስ በሚል። ሁለቱም የየራሳቸው ፓትሪያርክ አላቸው። ይህ ሁኔታ የሃይማኖቱን ተከታዮች ግራ መጋባትና መከፋፋል ውስጥ ከተቶ ቆይቷል።

በእስልምና ሃይማኖት ተቋም ውስጥም ችግር ተፈጥሮ ቆይቷል። በተለይ ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ወይም መጅሊስ ውስጥ ችግር አለ በሚል ይህን ለማስተካከል መነሳታቸውን ገልጸው በተደራጁ (መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ) አካላትና በሃላፊነት ላይ በነበረው መጅሊስ መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። የተፈጠረው አለመግባባት እልባት ሳያገኝ በመላ ሃገሪቱ በየደረጃው ያሉ የእስልምና ምክር ቤቶች አባላትና መሪዎች ምርጫ ተካሂዷል። ይህን ተከትሎ ከፍተኛ ተቃውሞ ተቀስቅሶ እንደነበረ፣ ተቃዋሚዎቹ መንግስትን በጣልቃ ገብነት ይከሱ እንደነበረም ይታወሳል። ከዚሁ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በርካቶች በቁጥጥር ስር ውለው በወንጀል ተከሰው እንደነበረም ይታወሳል፤ በጥፋተኝነት የተፈረደባቸውም ነበሩ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን መካከል እንደሆነው ሁሉ ይህ ሁኔታ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መሃከል መከፋፈልና መደናገርን ፈጥሮ መቆየቱ ይታወቃል።

ከመንፈሳዊ ህይወት አኳያ ሲታይ፣ በባህሪው ፍቅር፣ እርቅና ሰላም ከሆነው ምሉዕ በኩለሄ ፈጣሪ ጋር ሰውን እንዲያገናኙ የሚጠበቁት እነዚህ የሃይማኖት ተቋማት በራሳቸው ውስጥ እርቅ ማስፈን ባለመቻላቸው ምዕመናን በተቋማቱና በመንፈሳዊ አባቶቹ ላይ እምነት አጥተው ቆይተዋል። በውስጣቸው ያሉ ሹኩቻዎች ተቋማቱ ከመለኮታዊነት ይልቅ ምድራዊነታቸው እንዲጎላ ያደረገን ሁኔታ ስለፈጠረ ሰላምን፣ እርቅን፣ መቻቻልን የመስበክ መንፈሳዊም የሞራልም አቅማቸውም ደካማ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሁኔታ በተለያዩ ሰበቦች የሚነሱ ግጭቶችን ማስቀረት የሚችል ሞራል የመገንባት አቅም አሳጥቷቸዋል።

በሃይማኖት ተቋማቱ ውስጥ የተፈጠረውን አለመግባባት ከምድራዊ ህግና ስርአት አኳያ ስናየው በጥርጣሬ ለመተያየትና ለግጭት አመቺ የሆነ ሁኔታን ፈጥሯል። መለኮታዊ ባህሪያቸው ላይ አጥልቶባቸው ዓለማዊነታቸው እያመዘነ የሄደው የእምነት ተቋማቱ በምዕመናኑ መሃከል የፈጠሩት መከፋፈልና በጥርጣሬ መተያየት ነው ለግጭት አመቺ የሆነ ሁኔታን የፈጠረው። የተከፋፈሉት ወገኖች የፖለቲካ ቡድኖች መጠቀሚያ ለመሆን ተጋልጠው የነበሩበትን ሁኔታም ታዝበናል። በሃይማኖቶቹ ምዕመናን መሃከል የተፈጠረ መከፋፈል ወደ የብሄር እንዲሁም የፖለቲካ አመለካከት አለመገባባትና ግጭት የማደግ አቅም ማጎልበቱን የሚያሳዩ ምልክቶችም ተስተውለዋል።

የሃይማኖት ተቋማቱ የህዝቡን መንፈሳዊና ምድራዊ ህይወት የማገልገል መለኮታዊና የሞራል ግዴታ አለባቸው። በሃገሪቱ ሰላምን፣ እርቅን፣ መከባበርንና መቻቻልን እንዲሰብኩም ይጠበቃሉ። ይህ በመንግስትና በሃይማኖት ተቋማት መሃከል የጋራ ወሰን ነው። እንግዲህ በኢትዮጵያ ሁኔታ መንግስትና ሃይማኖት በህገመንግስት ተለያይተዋል። አንዱ በሌላው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አይገቡም። ይሁን እንጂ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ እርቅና ሰላምን የሚያፋልስ፣ ነጻነትን የሚገድብ፣ በአጠቃላይ ለህዝቡና ለሃገሪቱ ሰላም ስጋት የሚፈጥር ሁኔታ ሲያጋጥም መንግስት ይህን ሁኔታ በማስተካከል የተገደበ ጣልቃ ገብነት ሊኖረው ይችላል። በቅርቡ በእስልምና እና በኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ የተፈጠረውን ልዩነትና መቃቃር ለማስታረቅ በመንግስት የተወሰደው እርምጃ ይህን ታሳቢ ያደረገ ነው።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረውን መከፋፈልና አለመግባባት ለመፍታት የወሰኑት ከላይ በተገለጸው ምክንያት ነው። በሃይማኖቶቹ ውስጥ የነበራቸው ጣልቃ ገብነት ተቋማቱ ውስጥ የተፈጠረው ችግር በሃገሪቱና በህዝቡ ሰላምና ልማት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በማቃለል የተገደበ ነው።

እንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ በዚህ መሰረት በአስልምና እምነት ውስጥ፣ በእስልምና ጉዳዮች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴና በመጅሊሱ መሃከል ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት ሁለቱን አካላት አስታርቀዋል። ሁለቱ አካላት በእስልምና እምነት ተቋም ውስጥ አሉ የሚሏቸውን ችግሮች ተወያይተው የመፍታት እንቅስቃሴ ጀምረዋል። በየደረጃው ይህን ተግባር የሚያከናውን ኮሚቴ አዋቅረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በውጭና በሃገር ውስጥ ለሁለት ተከፍሎ የነበረውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስም አስታርቀዋል። ሁለቱ ሲኖዶሶች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡላቸውን የእርቅ ሃሳብ ተቀብለው እነሆ ራሳቸው ያለምንም ሽምጋይ ተማክረው ሲኖዶሱን አንድ አድርገው በውጭ ያለው ሲኖዶስ ከነፓትሪያርኩ ወደሃገር ቤት ተመልሷል።

ከላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ ታሪክና ስልጣኔ ውስጥ የጎላ ድርሻ ያላቸው፣ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተከታይ ያፈሩ ሃይማኖቶች ውስጥ የተፈጠረው እርቅ ሃይማኖቶቹ ፍጹም ፍቅር፣ ይቅርታና እርቅ መገለጫዎቹ የሆኑትን ምሉዕ በኩለሄ ፈጣሪ ቃል የመስበክ መንፈሳዊና የሞራል አቅም እንዲኖራቸው ያደርጋል። ይህ ሁኔታ በምዕመናኑ መሃከል ተፈጥሮ የነበረውን መከፋፈል በማስቀረት ለጥርጣሬና ግጭት ሰበብ ሊሆን የሚችለውን ሁኔታ ያስቀራል። በሃይማኖት ተቋማቱ ውስጥ የወረደው እርቅ ሰማያዊም ምድራዊም ፋይዳ ያለው ነው።